#ዘፍጥረት

#አጠቃላይ_መግቢያ

የዘፍጥረት መጽሐፍ በራሱ ማን እንደጻፈው አይጠቁምም። ቢሆንም ከጥንት ጀምሮ ይህ መጽሐፍ ሙሴ እንደጻፈው ነበር የሚታመነው። በእርግጥም ይህ አሳብ እንዲታመን ወሃ የሚቋጥር ምክንያት ነበራቸው። የቶራሕ ሌሎቹ መጽሐፎች ከዚህ መጽሐፍ ጋር ሃይለኛ ቁርኝት ስላላቸውና በሌሎቹ መጽሐፍትም የሙሴ ሥራና ስም በእጅጉ ስለተጠቀሰ ሙሴ የቶራሕ ጸሐፊ ወይንም ለመጽሐፉ ከማንም በላይ የቀረበ ሰው ነው ተብሎ ይታመን ነበርና ነው።

ሆኖም እንዲህ ዓይነት ምክንያቶችና ይህንንም የሚያንጸባርቁ ትውፊቶች ወደጎን ሲባሉ፣ ሌላ ብዙ ዓይነት የጥናት ዘዴዎች ብቅ ብቅ ሲሉ መሴ እነዚህን መጽሐፍት ጽፏቸዋል ለማለት የሚከብዱ ነገሮች ብቅ ብለዋል። ብዙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ተመራማሪዎች (አጥኚዎች) የመጽሐፉን አደረጃጀትና የጭብጥ አሠዳደርን ምንጭ በማጥናት፤ እንዲሁም በዘፍጥረት መጽሐፍት ላይ የተጠቀሱ (አስቀድሞ ክትውልድ ትውልድ በአፈ ታሪክ ይነገሩ የነበሩትን ጨምሮ ፣ በሌሎች አካባቢዎች እንዲህ ዓይነት ትርክት መኖሩን በማጤንና በማመሳከር) ጭብጦች ዘመናቸውን በማጤን ፣ እንዲሁም የነበረውን ትርክርት ያስቀመጡበትንና ያደራጁበትን ቋንቋ በማጤን - ይህ ሥራ ፍልሰት ከመሄዳቸው አስቀድሞ እስከ ከፍልሰት ተመልሰው በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው በማለት ያስቀምጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ የጥናት ሂደት “source criticism” ይባላል። በተጨማሪም ዘመነኛው ጥናት በ “ሪዳክሽን ክሪትሲዝም” (ይህ ማለት መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጭብጦች እንዴት መጽሐፍ እንደሆኑ ማጥናት ነው) ጥናቱ የዘፍጥረት መጽሐፍ ጭብጦች ከብዙ ምንጮች የተቀዱ እንደሆነ ማሳሳብ ጀምሯል። እንዲህ ዓይነቱ ክርክር እና ጥናቶች እየበረከቱ ባለበት ዘመን ላይ ነው አሁን ያለነው።

የሆኖ ሆኖ መጽሐፉን እንደ መጽሐፍ ማንም ያደራጀው ማንም (ሙሴም ይሁን ወይም ኢያሱ፤ በዳዊት ጊዜም ይደራጅ ወይንም በሰለሞን ጊዜ፤ ዕዝራም ይሥራው ወይንም ከምርኮ መልስ ያለ ሌላ ሰው) በውስጡ የሰፈረው ጭብጥ በአስራ አንድ ክፍል ተከፋፍሎ እናገኘዋለን፤ በእያንዳንዱም ክፍል መግቢያ “የ.... ልደት ወይንም ትውልድ እንዲህ ነበር” ቢመሚል የሚጀምር ነው። የመጀመሪያው በ 2፥ 4 ላይ የምናገኘው ሲሆን “እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን ባደረገ ቀን፥ በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር **ልደት** (toledoth) ይህ ነው።” የሚል ነው። የተቀሩት አሥሩ የትውልድ (toledoth) ክፍል ግን ግለሰቦች ላይ ያጠነጥናል - (አዳም፣ ኖህ፣ ሴም ... ወዘተ) ። እንደዚህ ዓይነት አሰዳደሮች ምናልባትም መጽሐፉን ያጠናከረው ሰው እነዚህን የትውልድ ዝርዝሮች ከተለያየ ምንጮች ማግኘቱን የሚያመላክት ሊሆን ይችላል። ሆኖም ከሙሴ አስቀድሞ ያሉ ትርክቶች እንደሆኑ አይጠፉንም።

1. #ታሪካዊ_ዳራ

#ጸሐፊው ወይንም #አዘጋጁ

1) ነባሩ አመለካከት ፥ - ምንም እንኳ የቶራሕ መጽሐፍቶች በሙሉ ጸሐፊያቸው ማን እንደሆነ በግልጽ ባይናገሩም ነባሩ ጥናትን ጠቅሰው ራይሞንድ ዲላርድ እና ትሬምፐር ሎንግማን የሚሏቸው ምሑራን በጋራ በሠሩት ጥናት (An Introduction to the Old Testament; Zondervan Publishing House, Grand Rapids, MI, 1994; p. 51.) የቀደመውን የአይሁድ ባሕልን እና የቀደሙትን ክርስቲያኖች ሥራ በማጣቀስ ከዘፍጥት እስከ ዘዳግም ድረስ የሙሴ ሥራ እንደሆነና አንድ ሌላ ሰው “ኤዲት” እንዳደረገው ይጠቁማሉ።

በተጨማሪም ፊሎ የሚባለው ፈላስፋ እና የታሪክ ዘጋቢ የነበረው ጆሴፈስ፤ እንዲሁም “ሚሻናህ” የሚባለው የአይሁድ የጽሑፍ ሥራዎች ጥንክር (እስከ 200 A.D. ዓመት ድረስ ያሉቱ) እና “ታልሙድ” የሚባለው በሚሻናህ ጥንቅር ውስጥ ያለ ከአይሁድ ትውፊቶች ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለው ሥራ - ቶራሕ በሙሉ የሙሴ ሥራ እንደሆነ አስቀምጠዋል።

ከዚህ ሁሉ ባሻገር የብሉይም ሆነ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ራሳቸው አምስቱን መጽሐፍት - “ቶራሕ”ን የሙሴ መጽሐፍት በማለት ይጠሯቸዋል፤ ለምሳሌ ማር. 12፥ 26 የ ዘጸ. 3፥ 6 ነጸብራቅ እንደሆነ፤ የሮሜ. 10፥ 5 ደግሞ የዘሌ. 18፥ 5 ነጸብራቅ እንደሆነ፤ የዕዝ. 6፥ 18 አሳብ የዘሕ. 3፥ 6 እንደሆነ፤ የማቴ. 19፥ 7 አሳብ ደግሞ የዘዳ. 24፥ 1 – 4 እንደሆነ መጠቆም ይቻላል።

ጌታችን ኢየሱስም የአይሁድ የብሉይ ኪዳንን አሠዳደር ተመርኩዞ (አይሁዶች የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን በሦስት ይከፍላሉ - ቶራህ፣ ኔቢም ፣ ኬቱቢም ብለው) የመጀመሪያውን አምስቱን መጽሐፍት በሙሴ ስም መጥራቱን ለማመሳከሪያነት ያመላክታሉ - ሉቃ. 24፥ 47። ጳውሎስም ቢሆን እነዚህን የቶራሕ መጻሕፍት በሙሴ ስም ሲጠራቸው የታየበት ክፍል አለ - ገላ. 4፥ 21 – 22 (ከ ዘፍ. 16፥ 15) ።

2) አዲሱ አመለካከት (ነባሩ አመለካከትን የሞገተ)

የመጽሐፉን ወጥነት ለመቀበል የሚቸገሩ ብዙ ምሑራን ቢኖሩም የመጀመሪያውና ታዋቂው ሞጋች ግን ፈላስፋው ባሮክ ስፒኖዛ (1632 – 1677) ነበር። እሱን በመከተል የሕክምና ባለሙያው ጄ. አስቱር (1684 – 1766) ነባሩን አመለካከት በመሞገት ተነሣ። አስቱር ዘፍጥረት ከሁለት ምንጮች የተቀዳ ሥራ እንደሆነ ያስብ ነበር። እነዚህም ምንጮች የለየበት መንገድ መጽሐፉ የአምላክን ስም በሁለት ዋና ዋና ስም በመጠቀሙ (ኤሎሂም እና ጆሆቫ) ከሁለት ቀደምት ሥራዎች እንደተቀዳ ወይም ሁለቱን ሥራዎች ያዋሃድ ሥራ ነው ብሎ ያስባል - ዘፍጥረትን። ከእርሱ በኋላም ብዙ ምሑራን እንዚህን ሁለት ምንጮች ምንና ማን እንደሆኑ እየተመራመሩ ቀጥለዋል።

በ 1880 ደግሞ ይህንን ምንጭን የማግኘት የምርምር ሥራን “በታሪካዊና ምርምራዊ የጥናት አቀራረብ” (historical-critical approach) ወደጫፍ አመጡት፤ ጄ. ኤች. ዌልሃንሰን በ 1883 ባሳተመው ሥራው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተነሳው ትውልድ የቀደመውን አመለካከት ጥርጣሬ ላይ እንዲጥል አድርጎታል።

ዌልሃንሰን አምስቱ መጽሐፍት ከአራት መሠረታዊና የተለያዩ ምንጮች የተጠናከረ እንደሆነ ያትታል። ምንጮቹንም የለየበት አራት መሥፈርቶች ነበሩት፤ እንደኛ፥ - የአምላክን ሥም በተለያየ መንገድ የጠቀሱቱ በማለት ነው (ኤሎሂም እና ጆሆቫ)፤ ሁለተኛ፥ - አንድን ትርክት ሁለት ጊዜ መጻፍን በተመለከተ (ለምሳሌ አብርሃም አቤሜሌክን ስለሚስቱ እንደ ዋሸ ሁሉ (ዘፍ. 12፥ 10 – 20) ሌላኛው ሰው (ይስሃቅ) እንዲሁ እንዳደረገ ተተርኳል (ዘፍ. 26፥ 1 – 11) ። ሦስተኛ ፥ - የአዘጋገብ ዘዬ (ስታየል)ን በተመለከተ ነበር (ለምሳሌ፥ - አንዳንድ ቦታ አጻጻፉ ኖርማል ዘገባ ሲሆን፤ አንዳንድ ቦታ የጥንት ሕጋዊ ጉዳዮችን የሚዘገብበትን ዘይ ይጠቀማል፤ እንዳንድ ቦታ ደግሞ በአደባባይ የሚነገሩ ገለጻዊ አካሄድን ተከትሏል)፤ አራተኛ፥ - የተለያዩ ስነ መለኮታዊ እይታዎች መታየታቸው አስመልክቶ ነው።

በእነዚህ የመለያ መንገዶች ዌልሃንሰን ፔንታቱክ የተዋቀረበትን ምንጮች በሚከተለው መንገድ አስቀምጧል፤ የመጀመሪያው ምንጭ “ጄ” ሲባል እርሱም የአምላክ ስም በጆሆቫ የተጠቀሰባቸውን ቦታዎች ከአንድ ምንጭ እንደተቀዱ ያስቀምጣል፤ ምንጨም የነበረው በዳዊትና በሰሎመን ዘመን በኢየሩሳሌም ነበረ ይለናል። ሁለተኛው ምንጭ ደግሞ “ኢ” በመባል ሲታወቅ እርሱም የአምላን ስም “ኤሎሂም” ተብሎ የተጠቀሰባቸውን ቦታዎች ይመለከታል፤ ይህ ምንጭ ደግሞ እስራዔል እንደመንግሥት ከተቋቋመች በኋላ (ከዳዊትና ከሠለሞን መንግሥት በኋላ) በሰሜናዊው አስራዔል አንድ ስፍራ እንደነበረ

ያትታል። ሦስተኛው ምንጭ “ዲ” በመባል የሚታወቅ ሲሆን በዘዳግም መጽሐፍ ላይ ለእስራዔላዊያኑ የተደገመውን አሳብ የሚያካትት ነው፤ ይህም ምንጭ በ 8 ኛውና በ 7 ኛው ክፍለዘመን (ከክርስቶስ ለልደት በፊት) እንደተሠራ የሚያትት ነው። አራተኛው ምንጭ “ፒ” የሚባል ሲሆን ስለ ካህናት የተጻፈውን ዝርዝር አሳቦች በሙሉ የሚያካትት ነው (በአብዛኛው ዘሌዋውያን የሚባለውን ክፍል)፤ ይሄም ምንጭ በምርኮ ዘመን ወይንም ከምርኮ እንደተመለሱ (550-450 B.C) እንደተዘጋጀ ይታሰባል።

በመጨረሻም በጽሑፍ ስራ እውቅ የሆነ ሰው አንድ ላይ እንዲሆኑ በማድረግና በማያያዝ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ (ወደ 400 ከክርስቶስ ልደት በፊት አካበቢ) ሠርቷቸዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

የሆኖ ሆኖ ይህ የማያባራ ክርክርና ጥናት እስካሁን ድረስ በወግ አጥባቂው ክርስትና ተቀባይነት አላገኘም። ዌልሃንሰንም ያነሣቸው አሳቦች ለአንድ ቅዱሳት መጽሐፍትን በአግባቡ ለሚያጠና ሰው ምንም አይረባምም ማለት አይቻልም።

#ተደራሲዎቹ እነማን ናቸው?

የመጨረሻው እንደመጽሐፍ የተዘጋጀውና የተበጀው ሥራ

- ሙሴ ነው ካልን - ከሲና ተራራ እንስቶ እስከ ሞዓብ ድረስ ባደረጉት ጉዞ መካከል ነው ተብሎ ይገመታል
- ከመርኮ በኋላ ከሆነ - የታደሰችውን እስራዔል ለማየት የሚናፍቀው ከምርኮ ተመላሽ ሕዝብ ነው ተብሎ ይታሰባል

2. #ስነጽሑፋዊው_ይዘትና_ቁመናው

የዘፍጥረት መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ሲሆን እርሱም “በመጀመሪያ” ብሎ ጽሑፉን የሚጀምር ነው። የምን መጀመሪያ የሚለው ጥያቄ እስካሁን ምሁራንን እያከራከረ ሲሆን፤ አንዳንዶች የሁሉ ነገር መጀመሪያ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ እስራዔል እንደ ሕዝብ ተመሥርቶ እግዚአብሔር ሊያወርሰው ያለውን ምድር ለመውረስ እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት የሁሉ ነገር መጀመሪያ ምን እንደሆነ ለማስረዳት ነው ይላሉ።

የዘፍጥረት መጽሐፍ በመጀመሪያ ደረጃ ስነ መለኮታዊ እና ታሪካዊ ትርክት እንደሆነ መታወቅ አለበት፤ ሆኖም ስነ መለኮታዊና ታሪካዊ ትርክትን ብቻ ሳይሆን በውስጡ የጥበብ (የቅኔ) አጻጻፍንም ይዟል - ዘፍ. 2፥ 23፤ 4፥ 23 (እንደውም አንዳንዶች ምዕ. 1 እና 2 ሙሉውን ይላሉ)፤ ትንቢትም ይዟል - 3፥ 15፤ 49፥ 1

ውስጡ በተለይም ከምዕ. 1 – 11 ያለው በቅርስ ቁፋሮ ከተገኘውእና 1900 – 1700 (ከክ.ል.በ.) እድሜ አለው ከሚባለው “ኢኑማ ኤሊሽ” ከሚባል ከመሶጵጣምያ የአፈጣጠር ታሪክ ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ነው ይባላል። በእርግጥ ሥራዎቹ “ያሕዌ” ይህንና ያንን አደረገ የሚሉ ሳይሆኑ “መድሩክ” (የባቢሎኑ አማልክት) የፈጠረውን አደራረግ የሚተርኩ ናቸው።

የኖህ የጥፋት ውሃ ትርክት እንዲሁ በሱሜሪያኖች የጥንት ጽላት ላይ ተቀርጾ ተገኝቷል፤ ምናልባትም ይህ ጽላት ወደ 1600 ዓመት (ከክ.ል.በ.) ስለሚመጣው የትፋት ውሃ ተጠቅሶ ተገኝቷል። ይህ የጥፋት ውሃ እንዲሁ በገልገሚሽ የባቢሎናውያን የጥንት ታሪክ መዘገቢያ የተጻፈ እንደሆነ እየተገለጠ ነው - 2500 – 2400 ከክ.ል.በ.

እንዲሁም የሰው ልጆች እንዴት ከአንድ ቦታ ወደ ስፍራ ሁሉ እንደተበተኑ (ልክ በዘፍ. 10 – 11 እንዳለው) እና የመበተናቸው ምክንያት ደግሞ የሰው ልጆች ከቅድመ ጥፋት ውሃ አስቀድሞ በላቸው እውቀትና ከአምላክ ጋር ባላቸው ግንኙነት እንደሆነ በትይዩነት የዘገቡ የጥንት ሥራዎች አሉ፤ ይሄ ደግሞ የዘፍ 2. እና የዘፍ. 6 ን አሳብ ያስታውሰናል።

የጥንት ግብጻውያንን የፍጥረት ትርክት ስናይ ልክ እንደ ዘፍጥረቱ ሁሉ ፍጥረት ከቅርጽ አልባነት፣ ከጨለማ፣ ከፍጥረቱ በፊት ከነበረ ውሃ እንደሚነሣ የሚተርክ ነው።

#ዓላማው፥ -

እስራዔላውያኖች ለራሳቸው ያለው መረዳትና እና ሥነመኮታዊ ንጽረተ ዓለማቸውን መቅረጽ ሲሆን በዚህም ለሕዝብ ሁሉ የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማገልገል እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው፤ ይህንንም የዘፍጥረት መጽሐፍ አዘጋጅ እግዚአብሔር - ንጉሱ እንዴት ለሌላው ሕዝብ ይተርፉ ዘንድ እንደመረጣቸው (12 – 50) በማሳየት እና ለውደቀትና ለእርግማን እንዲሁም ለውድቀት ለተበላሸ ሕዝብ የመለሰውን በማሳየት ነው (1 – 11)።

#ማውጫ

መጽሐፉ በአጠቃላይ በሁለት ይከፈላል፤ እግዚአብሔር እና የሰው ዘር የሚለው ከ 1 – 11 ያለው ሲሆን፣ እግዚአብሔርና አስራዔል ደግሞ ከ 12 – 50 ተዘጋጅቷል።

ማን ጻፈው?	**እግዚአብሔር እና ሰው (1 – 11)**	**መካከለኛ**	**እግዚአብሔር እና አስራዔል**
የሙሴ ቶራሕ ጸሐፍት በዘመናት ሁሉ እያጠናከሩት “ታናክ”ን አዘጋጁልን **ዓለማውስ?** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለተዘገበው ለእግዚአብሔርና ሰው ግንኙነት ጥልቅ መግቢያ መስጠት ሰው የተፈጠረለትን ዓላማ ማሳየት የእስራዔላውያንን የመነሻ	ከጨለማና ከጥፋት - - - ፍጥረት - - - እግዚአብሔርና ፍጥረቱ የሚገናኙበት ቦታ (ገነት እንደ መቅደስ 1 ፥ 1 – 2 ውድቀት - እርግማን ተስፋ - 3፥ 15 እንደገና ፍጥረት - ከትፋ ውሃ ውስጥ - ድነት ኖህ ራቁት ሆነ እንደ አዳምና ሄዋን 7፥ 1 - 9፥ 17 ሕዝቦችና የራሳቸው መንገድ (ክፉና ደግን የማወቅ ፍሬ ውጤት	**ለአብርሃም የተሰጠ ተስፋ** **12፥ 1 – 3** የእግዚአብሔር መገኘት ዘሮቹ መሬት	አብርሃም - በእግዚአብሔር ተጠራ • በምድርም ዞረ • በእግዚአብሔር ተፈተነ • እግዚአብሔርን አመነ • ዘፍ. 12 – 24 **ልክ አስራዔል መሬቱን ከመያዙ በፊት እንደነበረው ሕይወት** **ይስሃቅ** - በተስፋይቱ ምድር ተቀመጠ • መቶ እጥፍ ተባረከ • ዘፍ. 25 – 27 ልክ አስራዔል የተስፋይቱን እንደወረሰና መንግሥት ሆኖ ይኖር እንደነበር **ያዕቆብ** - አታላ ተብሏል • ወደ ምስራቅ ተሰደደ • እግዚአብሔርም ስሙን

ታሪክ ማሳየት ለሕዝብ ሁሉ ያለውን ተስፋ ማሳየት	- ዘፍ.3) ባቤል - የሰዎች መቅደስ (የኤደን ገነት ተቃራኒ) 9፥ 18 - 11፥ 32		ለወጠ በታገለው ጊዜ • ያዕቆብ እስራዔል ሆነ ልክ አስራዔል ወደ ምሥራቅ እንደተሰደደ እና ወደ ቤቱ እንደተመለሰ **12 ነገድ ምዕ 37 – 50** ሁለት ነገድ ላይ ያተኩራል የሴፍ እና ይሁዳ ላይ የሴፍ ልክ የሕዝብ ሁሉ ታዳጊ እንደሚመስል ይሁዳም የሕዝብ ሁሉ ንጉስ ሆኖ ነው የተሳለው

3. #ሰነ_መለኮታዊው_ፋይዳ

1) የፍጥረት መጀመሪያ

ፍጥረት ከየት እንደጀመረና እንደመጣ እንዲሁም ለምን ዓላማ እንደተፈጠረ ለአማኙ ማሕበረሰብ ከሳይንስና ከአፈ ታሪኮች እንዲሁም ከፍልስፍናው በላይ ይህ መጽሐፍ ያስተምረናል። ሆኖም የዘፍጥረት ዘገባ ሳይንሳዊ ማስረጃን ለመሞገት የተጻፈ ስለሆነ ከምክንያታዊነት በፊት እምነት እንደሚቀድም ማወቅ ያስፈልጋል። የሁሉ ነገር መጀመሪያና የመጀመሪያን ዓላማ እንዲሁም በምን ምክንያት ፍጥረት እንደተፈጠረ ወይም እግዚአብሔር እንደፈለገው እንዳልሄደ የሚጠቁመን መጽሐፍ ነው።

2) ውድቀት - ኃጢአት

የዘፍጥረት መጽሐፍ አንዱ ሊነግረን የፈለገው ጭብጥ አሁን ባለነው ዓለም ያለን ክፋትና ጥላቻ እንዲሁም ግራ መጋባት፤ ሞት ጥፋትና እልቂት ... ወዘተ እንዴት እንደጀመረ ለመጠቆም ነው። የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች እንዴት በሴጣን መታለል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ዓላማ እንደወደቁና በራሳቸው ለመኖር የታገሉት ወይንም የሞከሩት ሕይወት በዓለም ላይ ላይ ላይ ጥፋትና ውድቀት እንዲሁም ሞት ምክንያት እንደሆነ ይጠቁመናል። አዳምና ሄዋን የሰውን ዘር ሁሉ በወገባቸው ይዘው (ባለመታዘዛቸው ምክንያት) ከእግዚአብሔር መገኛ ወጡ፤ በራሳቸውም መንገድ መመለስ እንዳይችሉ የሆነውን ፍረድ ያስነብበናል። ብቸኛው የድነትና የትድግናን ተስፋም ይጠቁመናል - የቆሰለው ታዳጊ እንደሚመጣና የጠላትን ራስ ቀጥቅጦ የሰው ዘርን እንደሚታደግ ተስፋ ይዘው ከኤደን ወጡ።

3) የትድግና መንገድ - የአብርሃም መመረጥ

የዘፍጥረት መጽሐፍ አምላክ የወደቀውን ሰው በራሱ መንገድ ወደ ተፈጠረለት ዓላማ ይመለስ ወይም በራሱ መንገድ ካለበት ማጥ ውስጥ ይውጣ ብሎት ሲተወው አናይም፤ ይልቅኑ የትድግናውን መንገድ አንድን ሰው በመምረጥ ሲጀምር እናያለን - አብርሃምን በመጥራት። አብርሃም ከሰዎች ሁሉ ለየት ያለ ሰው ስለሆነ እና ከሌላው ይልቅ የመጠራት ብቃት ስላለው አይደለም የተጠራው - ይልቅ ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሆነ እናያለን። በዚህም የትድግና ጥሪ የማዱኑን ዓላማ ለመፈጸም እንጂ ባልተጠራው ወገን ላይ ብልጫ እንድንይዝ እንዳልሆነ ያስረዳል። አብርሃምን ተከትሎ አስራዔል ለዚህ በጎ ተግባር ጥሪው ደርሷት ተመርጣ ነበር - "የንጉስ ካህን" እና "የተመረጠ ቅዱስ ሕዝብ " ተብለው ነበር። ሆኖም የጥሪያቸውንና የመመረጣቸውን ዓላማ በመሳት ራሳቸውን ብቻ እንደልዩ ሕዝብ ሲያዩ እንዴት በውደቀትና በፍልሰት እንደጨረሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።